በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:-** kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ኅዳር ፳፫ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም.

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

- በምዕራፍ አሥራ አንድ የምንማረው በቁጥር የሚበዙት አይሁድ ከኢየሩሳሌም ከተማ ውጪ ይኖሩ የነበር ቢሆንም ኢየሩሳሌምን ይዘው በቁጥር ለመብዛት እንዲቻላቸው ከአሥሩ አንድ አንድ እየመረጡ እንዲኖሩ ሲያደርጉ በከተማዋ የተቀሩት በሌሎች ከተሞች እንዲኖሩ ዕጣ ተጣጣሉ።
- አንዳንዶችም የተቃጠለውን የከተማዋን ክፍል እያዩ ለመኖር የማይፈቅዱ ሆኑ። ይህ የሚያስተላልፍልን መንፈሳዊ መልእክት አንዳንድ ሰዎች ከኀሊናቸውና ከመንፈስ ቅዱስ ወቀሳ ለማምለጥ ሲሉ በቤተ ክርስቲያን መኖር የማይሹ መሆናቸውን ነው። በኢየሩሳሌም የኖሩት ግን መንፈሳዊውን ተግባር ከማከናወን ጋር የቀደመውን ሥርዓት ጠብቀው ይመላለሱ ነበር።
- በዚህ ምዕራፍ የተጻፉት ስሞች የሚያስታውሱን በሕይወት መጽሐፍ የተጻፉትን ነው፤ ዛሬም ከእግዚአብሔር ጋር የምንኖረው መጨረሻችን ሰማያዊቱን ኢየሩሳሌምን መውረስ ነው።
- ስማቸውም የተጻፈበት ቅደም ተከተል በመሪዎች ጀምሮ፣ ሌዋውያንን፣ የቤተ መቅደሱን ጠባቂዎችና አገልጋዮች የተከተለ ሲሆን ይህም በሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም እያንዳንዱ ወገን የሚኖረውን መንፈሳዊ ማዕረግ (ደረጃ) የሚያመለክት ነው።
- ምዕራፍ አሥራ ሁለት ከ 1 እስከ 26 ድረስ ወደ ኢየሩሳሌም የገቡት ስማቸው ተጽፏል። የቅጥሩን ሥራ ፈጽመው ከሥርዓታቸው ጋር ባደረጉት በዓል ቅጥሩን ቀደሱት።
- ‹‹የኢየሩሳሌምንም ቅጥር በቀደሱ ጊዜ ቅዳሴውን በደስታና በምስጋና በመዝሙርም በጸናጽልም በበገናም በመሰንቆም ለማድረግ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጡአቸው ዘንድ ሌዋውያኑን በየስፍራቸው ሁሉ ፈለጉ። መዘምራኑም በኢየሩሳሌም ዙሪያ መንደሮች ሠርተው ነበርና የመዘምራኑ ልጆች ከኢየሩሳሌም ዙሪያና ከነጦፋውያን መንደሮች፥ ከቤትጌልገላም፥ ከጌባና ከዓዝሞት እርሻዎች ተሰበሰቡ። ካህናቱና ሌዋውያኑም ራሳቸውን አነጹ ሕዝቡንም በሮቹንም ቅጥሩንም አነጹ። የይሁዳንም አለቆች ወደ ቅጥሩ ላይ አወጣኋቸው አመስጋኞቹንም በሁለት ታላላቅ ተርታ አቆምኋቸው አንዱም ወደ ቀኝ

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

- በቅጥሩ ላይ ወደ ጕድፍ መጣያው በር ሄደ። ከእነርሱም በኋላ ሆሻያ፥ የይሁዳም አለቆች እኩሌታ፥ ዓዛርያስ፥ ዕዝራ፥ ሜሱላም፥ ይሁዳ፥ ብንያም፥ ሸማያ፥ ኤርምያስ፥ መለከትም ይዘው ከካህናቱ ልጆች አያሌዎች፥ የአሳፍም ልጅ የዘኩር ልጅ የሚካያ ልጅ የመታንያ ልጅ የሸማያ ልጅ የዮናታን ልጅ ዘካርያስ፥ ወንድሞቹም ሸማያ፥ ኤዝርኤል፥ ሚላላይ፥ ጊላላይ፥ መዓይ፥ ናትናኤል፥ ይሁዳ፥ አናኒ የእግዚአብሔርን ሰው የዳዊትን የዜማውን ዕቃ ይዘው ሄዱ ጸሐፊውም ዕዝራ በፊታቸው ነበረ። በምንጭም በር አቅንተው ሄዱ በዳዊትም ከተማ ደረጃ፥ በቅጥሩም መውጫ፥ ከዳዊትም ቤት በላይ እስከ ውኃው በር ድረስ በምሥራቅ በኩል ሄዱ። ሁለተኛውም የአመስጋኞቹ ተርታ ወደ ግራ ሄደ እኔና የሕዝቡም እኩሌታ በስተኋላቸው ነበርን በቅጥሩም ላይ፥ በእቶኑ ግንብ በላይ እስከ ሰፊው ቅጥር ድረስ፥ ከኤፍሬምም በር በላይ፥ በአሮጌው በርና በዓሣ በር በሐናንኤልም ግንብ፥ በሃሜአ ግንብ እስከ በጎች በር ድረስ ሄዱ በዘበኞችም በር አጠገብ ቆሙ። እንዲሁ ሁለቱ የአመስጋኞች ተርታዎች በእግዚአብሔር ቤት ቆሙ ከእነርሱም ጋር እኔና የአለቆች እኩሌታ፥ ካህናቱም ኤልያቄም፥ መዕሤያ፥ ሚንያሚን፥ ሚካያ፥ ኤልዮዔናይ፥ ዘካርያስ፥ ሐናንያ መለከት ይዘው፥ መዕሤያ፥ ሸማያ፥ አልዓዛር፥ ኦዚ፥ ይሆሐናን፥ መልክያ፥ ኤላም፥ ኤጽር ቆምን፡- መዘምራኑም በታላቅ ድምፅ ዘመሩ፥ አለቃቸውም ይዝረሕያ ነበረ።›› ***ነህ 12፡27-42፡፡***
- **ነህምያ ቅጥሩን ለመመረቅ ውብ የሆነው ሥርዓት ምን እንደሆነ አስተማረን፡፡ ካህናቱ፣ ምስጋና (ዝማሬ) የሚያሰሙት መዘምራኑ፣ ሌዋውያኑም (መዘምራኑና ዲያቆናቱ) በኢየሩሳሌም ዙሪያ ካሉት አውራጃዎች ሁሉ ተሰበሰቡ፡፡ እነዚህንም ነህምያ በሁለት ከፈላቸው፡፡**
- **ከቅጥሩ በአንድ በኩል የነበሩት በስም ከተጠቀሰው ከካህኑና ጸሐፊው ከዕዝራ ጋር ሌዋውያንና የይሁዳ ግማሾቹ መሪዎች ነበሩ፡፡**
- **ከቅጥሩ ሌላኛው በኩል የነበሩት ደግሞ ስማቸው ከነህምያ (ነህምያ ቂጥሩ ከካህናት ወይም ከሌዋውያን ባይሆንም) ጋር የተጠቀሱት ካህናትና ገዢዎች ነበሩ፡፡**
- **የተሰበሰቡትም በቅጥሩ ዙሪያ ከበው ዛሬ በቤተ ክርስቲያን እንደምናደርገው እየተቀባበሉ ዘመሩ፡፡ ቅጥሩም የምስጋናና የጸሎት ቅጥር ሆነ፡፡ - እኛንም የምንሠራውን ማንኛውንም ሥራ ሁሉ ለእግዚአብሔር መመስገኛ ለማድረግ ያብቃን፡፡ አሜን፡፡**

# <u>መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲</u>

***<u>የእግዚአብሔር ሰውና የዳዊት የዜማ ዕቃ</u>***

- በመዝሙር 150 እንደምናገኘው ዳዊት ይዘምርና ያመሰግንበት የነበረውን መንፈስና መንገድ ተከትለው ዘመሩ። ቅዱስ ዳዊት ***<u>በመዝ 150፡1-6</u>*** ‹‹… በመለከት ድምፅ አመስግኑት በበገናና በመሰንቆ አመስግኑት። በከበሮና በዘፈን አመስግኑት በአውታርና በእምቢልታ አመስግኑት። ድምፁ መልካም በሆነ ጸናጽል አመስግኑት እልልታ ባለው ጸናጽል አመስግኑት።እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን፡- ሃሌ ሉያ።›› እንደገለጸልን እነዚህን ሁሉ የዜማ ዕቃዎች ተጠቅመው ዘመሩ - እነዚህም የዳዊት የዜማ ዕቃዎች ናቸው።
- ‹‹እግዚአብሔርም በታላቅ ደስታ ደስ አሰኝቶአቸዋልና በዚያ ቀን ትልቅ መሥዋዕት አቀረቡ፥ ደስም አላቸው ሴቶቹና ልጆቹም ደግሞ ደስ አላቸው የኢየሩሳሌምም ደስታ ከሩቅ ተሰማ።›› ***<u>ነህ 12፡43።</u>***
- ቀኑን ሁሉ እያመሰገኑ መሥዋዕት አቀረቡ፤ መሥዋዕቱም የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው መሥዋዕታችን እርሱ ነውና፤ ደሙ ዘወትር በመሠዊያው ይፈሳል እኛም በርሱ ከኃጢአታችን እንነጻለን፡ ክብርና ምስጋና አምልኮትና ስግደት ለእርሱ ይሁን።
- የተሰው እንስሳትን ደም በመቃን ላይ መቀባት የክርስቲያኖች ሥርዓት አልነበረም፤ ዛሬም ይህን ማድረግ ዋጋ የሌለውና ከንቱ ነው፤ የምንኖረው በጌታችን በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነውና፤ በርሱም ፈጽመን እናምናለንና፤ ሥጋውን እንብላ ደሙንም እንጠጣ።

***<u>የኢየሩሳሌምም ደስታ ከሩቅ ተሰማ</u>***

- ይህም በዕለተ ሆሳዕና የተደረገውን ያስታውሰናል። ጌታችንን ተከትለው ‹‹ሆሳዕና በአርያም›› እያሉ ከደስታቸው የተነሳ አሰምተው ይዘምሩ የነበሩ ክርስቲያኖች ድምጽ ከሩቅ ይሰማ ነበርና። ***<u>ማቴ 21፡1-10።</u>***

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

- ‹‹ ይሁዳም በአገልጋዮቹ ካህናትና ሌዋውያን ደስ ስላላቸው፥ የካህናቱንና የሌዋውያኑን እድል ፈንታ እንደ ሕጉ ከከተሞች እርሻዎች ያከማቹ ዘንድ ለእጅ ማንሣት ቍርባንና ለበኵራት ለአሥራትም በየዕቃ ቤቶቹ ላይ በዚያ ቀን ሰዎች ተሾሙ።›› ***ነህ 12፡44፡***
- ነህምያ ሁሉን ማከናወኑን በመመርመር ለእያንዳንዱ ነገር ሥርዓት በማበጀት ሥራውን የሚከታተሉ መሪዎችን ሾመ፡፡
- ነህምያ ጊዜው አጭር እንደሆነ ፈጥኖም ወደ ሱሳ ተመልሶ የጠጅ አሳላፊነት ሥራውን መቀጠል እንዳለበት ስለሚያውቅ እርሱ በማይኖርበት ጊዜም ሳይቀር ነገሮች ተስተካክለው እንዲከናወኑና እንዲቀጥሉ ፈለገ፡፡
- ይህም አንድ ቀን እንደማይኖርና እርሱ በሌለበትም አገልግሎቱ እንዲቀጥል የሚያስብ አገልጋይ መታወቂያ ምልክት ነው፡፡ እንደ ነህምያ ያለም አገልጋይ ሥራዎችን በማከፋፈል ሌሎች በሚሠሩት ሥራ ደስ ይለዋል እንጂ ሁሉንም ነገር ራሱ ብቻ አይፈጽመውም፡፡
- ‹‹እነርሱም መዘምራኑና በረኞቹም የአምላካቸውን ሥርዓት የመንጻታቸውንም ሥርዓት እንደ ዳዊትና እንደ ልጁ እንደ ሰሎሞን ትእዛዝ ጠበቁ። አስቀድሞም በዳዊትና በአሳፍ ዘመን እግዚአብሔርን በዜማ ለማመስገንና ለማክበር የመዘምራን አለቆች ነበሩ።›› ***ነህ 12፡45-46፡፡***
- ነህምያ ቤተ መቅደሱ ከመሠራቱ በፊት በሰሎሞን ዘመን በተሠራው ቤተ መቅደስና ከዚያም በፊት በደብተራ ኦሪት ከዳዊት ዘመን ጀምሮ የነበሩትን ጥንትዊ መዝሙራት በማምጣት ቀንና ሌሊት የእግዚአብሔር ምስጋና የሚቀርብበትን መንገድ ሁሉ አመቻቸ፡፡ አሁንም ቀንና ሌሊት በቤተ ክርስቲያን የምንቀበለው አገልግሎት ከዚሁ የተወሰደ ነው፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

- ‹‹ዳዊትና የሠራዊቱ አለቆችም ከአሳፍና ከኤማን ከኤዶታም ልጆች በመሰንቆና በበገና በጸናጽልም ትንቢት የሚናገሩትን ሰዎች ለማገልገል ለዩ በአገልግሎታቸውም ሥራ የሠሩ ሰዎች ቍጥር ይህ ነበረ። ከአሳፍ ልጆች ዘኩር፥ ዮሴፍ፥ ነታንያ፥ አሸርኤላ እነዚህ የአሳፍ ልጆች በንጉሡ ትእዛዝ ትንቢት ከተናገረው ከአሳፍ እጅ በታች ነበሩ። ከኤዶታም የኤዶታም ልጆች ጎዶልያስ፥ ጽሪ፥ የሻያ፥ ሰሜኢ፥ ሐሸብያ፥ መቲትያ፥ እነዚህ ስድስቱ ለእግዚአብሔር ምስጋናና ክብር በመሰንቆ ትንቢት ከተናገረው ከአባታቸው ከኤዶታም እጅ በታች ነበሩ። ከኤማን የኤማን ልጆች ቡቅያ፥ መታንያ፥ ዓዛርኤል፥ ሱባኤ፥ ኢያሪሙት፥ ሐናንያ፥ ሐናኒ፥ ኤልያታ፥ ጊዶልቲ፥ ሮማንቲዔዘር፥ ዮሽብቃሻ፥ መሎቲ፥ ሆቲር፥ መሐዝዮት እነዚህ ሁሉ ቀንደ መለከቱን ከፍ ያደርጉ ዘንድ በእግዚአብሔር ቃል የንጉሡ ባለ ራእይ የሆነው የኤማን ልጆች ነበሩ። እግዚአብሔርም ለኤማን አሥራ አራት ወንዶች ልጆችንና ሦስት ሴቶች ልጆችን ሰጠው። እነዚህ ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት በጸናጽልና በበገና በመሰንቆም ይዘምሩ ዘንድ፥ በእግዚአብሔርም ቤት ያገለግሉ ዘንድ ከአባታቸው እጅ በታች ነበሩ አሳፍም ኤዶታምም ኤማንም ከንጉሡ ትእዛዝ በታች ነበሩ።›› ***ቀዳ ዜና 25:1-6::***
- ‹‹እስራኤልም ሁሉ በዘሩባቤልና በነህምያ ዘመን ለመዘምራኑና ለበረኞቹ እድል ፈንታቸውን በየዕለቱ ይሰጡ ነበር የተቀደሰውንም ነገር ለሌዋውያን ሰጡ፥ ሌዋውያኑም ከተቀደሰው ነገር ለአሮን ልጆች ሰጡ።›› ***ነህ 12:47::***
- **የተቀደሰውንም ስጦታቸውን ለሌዋውያን ሰጡ፣ ሌዋውያኑም ለካህናት ሰጡ፤ ካህናትም መሥዋዕትን የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸውና ከፍ አድርገው አቀረቡት፡፡**
- **በቃል የሚጠና ጥቅስ** ‹‹እግዚአብሔርም በታላቅ ደስታ ደስ አሰኝቶአቸዋልና በዚያ ቀን ትልቅ መሥዋዕት አቀረቡ፥ ደስም አላቸው ሴቶቹና ልጆቹም ደግሞ ደስ አላቸው የኢየሩሳሌምም ደስታ ከሩቅ ተሰማ።›› ***ነህ 12:43::***

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

- ‹‹በዚያም ቀን የሙሴን መጽሐፍ በሕዝቡ ጆሮ አነበቡ አሞናውያንና ሞዓባውያንም ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ ለዘላለም እንዳይገቡ የሚል በዚያ ተገኘ።›› ***ነህ 13፡1፡፡***
- በመጽሐፈ ነህምያ የመጨረሻ ምዕራፍ በርካታ ለውጦች ታይተዋል፡፡ የሙሴን መጽሐፍ ሲያነቡ አዲስ ነገር አገኙ፡፡ ይህም ብዙ የምናነብና የምናውቅ ነገር ግን ምንም የማንሰራውን እኛን የሚያስተምረን ነው፡፡
- እነዚህ ሕዝቦች ግን መንፈሳዊ ቅንዓት ስለነበራቸው ስለ አዲስ ነገር (ሕግ/ትእዛዝ) ሲያነቡ ያንን በሕይወታቸው በተግባር ያውሉት ስለነበር በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ፈጥነው ለውጥ አሳይተዋል፤ ይህም የተደረገላቸው ለእግዚአብሔር ትእዛዝ (ሕግ) ታዛዦች ስለነበሩ ነው፡፡
- አሞንና ሞዓብ በብሉይ ኪዳንና በአይሁድ ታሪክ ውስጥ የምናገኛቸው ሁለት አስቸጋሪ ሰዎች ናቸው፡፡ ***በዘፍጥ 19፡30-38*** ፡፡ እንደተጻፈልን ሎጥ አባታችን አብርሃምን ትቶ ወደ ሰዶምና ገሞራ ሄዶ በዚያም ሚስቱን ሳይቀር አጣ፤ ሰዶምና ገሞራም ተቃጠለች፡፡
- የሎጥ ሁለት ልጆቹ በሰዶምና ገሞራ ከሚኖሩ ኢአማንያን ተፈጥሮአዊ ባልሆነ መንገድ የግብረ ሥጋ ግኑኝነት መፈጸምን እየተማሩ ያደጉ በመጥፎ ሰዎችና መጥፎ በሆነ አካባቢ መካከል የኖሩ ስለነበሩ ድርጊታቸው ከፋ፡፡
- አባታቸውንም አጠጥተው ከሰከረ በኋላ አብረውት በመተኛት ከባድ ኃጢአት ፈጸሙ፡፡ በዚህም የተነሳ ከአባታቸው ጸንሰው አንዳቸው አሞንን ሌላኛዋ ሞዓብን ወለዱ፡፡ የአሞንና የሞዓብ ልጆችም ወደዚህች ዓለም ክፋትን በመሥራት በኢአማንያን መንገድ መጥተዋልና የክፋት ምልክት ሆነው ተቆጠሩ፡፡
- በአይሁድና በነዚህም መካከል ዘወትር መከፋፋት ነበር፡፡
- አይሁድ ከእግዚአብሔር መንገድ ሲወጡ ወደ ጎረቤቶቻቸው በመሄድ ከአሞናውያንና ከሞዓባውያን ሴቶችን ወስደው በማግባት ከመንፈሳዊ ሕይወትን ከመምራት ወጥተው ነበር፡፡ ከ400 ዓመታት በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን አሞናውያንና ሞዓባውያን ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር እንዳይቀላቀሉ አዞት ነበር፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

- ‹‹የእስራኤልን ልጆች በእንጀራና በውኃ ስላልተቀበሉአቸውና ይረግማቸው ዘንድ በለዓምን ስለ ገዙባቸው ነው ነገር ግን አምላካችን እርግማኑን ወደ በረከት መለሰው።›› ***ነህ 13፡2፡፡***
- የሞዓብና የአሞን ልጆች በእግዚአብሔር ሕዝቦች በእስራኤል ላይ ክፋትን በመጠንሰስ በሙሴ ዘመን በሲና በረሐ ያደረጉትንም ጉዞ ለማደናቀፍ ሞክረው ነበር፡፡ ይህም ***በዘኍልቍ 22፣ 23 እና 24*** ተገልጾ እናገኘዋለን፡፡
- የሞዓብ ንጉሥ ባላቅ ቁጥራቸው ብዙ የሆኑ ወደ ምድረ ርስት የሚጓዙ እስራኤላውያን ወደ መንደሩ እንደተጠጉ ሲሰማ ተጨንቆ ወደ በለዓም ‹‹እነሆ፥ ከግብፅ የወጣ ሕዝብ አለ እነሆም፥ የምድሩን ሁሉ ፊት ሸፈነ፥ በአቅራቢያችንም ተቀምጦአል አሁንም ይህ ሕዝብ ከእኔ ይበልጣልና ልወጋቸውና ከምድሪቱ ላሳድዳቸው እችል እንደ ሆነ፥ እባክህ፥ ና ርገምልኝ አንተ የመረቅኸው ምሩቅ የረገምኸውም ርጉም እንደ ሆነ አውቃለሁና ብሎ ይጠሩት ዘንድ መልእክተኞቹን ላከ።›› ***ዘኍ 22፡6፡፡***
- በለዓምም እግዚአብሔር ‹‹ከእነርሱ ጋር አትሂድ የተባረከ ነውና ሕዝቡን አትረግምም።›› ***ዘኍ 22፡12፡፡*** ያለውን አስቦ እምቢ አለ፡፡
- ባላቅም ዳግመኛ በለዓምን አስጠርቶ ቢጠይቀውም እግዚአብሔር ‹‹ሰዎቹ ይጠሩህ ዘንድ መጥተው እንደ ሆነ፥ ተነሣ ከእነርሱም ጋር ሂድ ነገር ግን የምነግርህን ቃል ብቻ ታደርጋለህ። ›› ***ዘኍ 22፡20፡*** ስላለው ወጥቶ ሄደ፡፡ በሄደበትም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አራት ጊዜ ቢመርቃቸውም በመጨረሻ የሞዓቡ ንጉሥ ሕዝቡን ከአሕዛብ ሴቶች ጋር በዝሙት ወድቀው እግዚአብሔር እንዲያጠፋቸው ምክር ሰጠ፡፡ ይህም የበለዓም ምክር ክፉና መራር ብሎም አጥፊ ነበር፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

- ‹‹ሕጉንም በሰሙ ጊዜ ድብልቁን ሕዝብ ሁሉ ከእስራኤል ለዩ።›› ***ነህ 13፡3፡፡***
- ሕዝቡም ሕጉ ምን እንደሚል ሲሰሙ ሞዓባውያንና አሞናውያንን ከመካከላቸው ለዩ፡፡
- ‹‹ ከዚህም አስቀድሞ በአምላካችን ቤት ጓዳዎች ላይ ተሾሞ የነበረው ካህኑ ኤልያሴብ ከጦቢያ ጋር ተወዳጅቶ፥ ለሌዋውያን፥ ለመዘምራን፥ ለበረኞቹ እንደ ሕጉ የተሰጣቸውን የእህሉን ቍርባንና ዕጣኑን፥ ዕቃዎቹንም፥ የእህሉንና የወይኑን የዘይቱንም አሥራት፥ ለካህናቱም የሆነውን የማንሣት ቍርባን አስቀድሞ ያስቀመጡበትን ታላቁን ጓዳ አዘጋጅቶለት ነበር። እኔ ግን በባቢሎን ንጉሥ በአርጤክስስ በሠላሳ ሁለተኛው ዓመት ወደ ንጉሡ ሄጄ ነበርና በዚህ ጊዜ በኢየሩሳሌም አልነበርሁም። ከጥቂት ዘመንም በኋላ የንጉሡን ፈቃድ ለመንሁ ወደ ኢየሩሳሌምም መጣሁ ኤልያሴብም በእግዚአብሔር ቤት አደባባይ ለጦብያ ጓዳውን በማዘጋጀት ያደረገውን ክፉ ነገር አስተዋልሁ። እጅግም አስከፋኝ የጦብያንም የቤቱን ዕቃ ሁሉ ከጓዳ ወደ ውጪ ጣልሁ። ጓዳዎቹንም እንዲያነጹ አዘዝሁ የእግዚአብሔርንም ቤት ዕቃዎች የእህሉንም ቍርባን ዕጣኑንም መልሼ በዚያ አገባሁ።›› ***ነህ 13፡4-9፡፡***
- ነህምያ ሁሉን አስተካክሎ መልክ አስይዞ ሥርዓት ዘርግቶ ልቡ በኢየሩሳሌም ቢቀርም በአካል ግን ወደ ባቢሎን ንጉሥ ወደ አርጤክስስ ተመልሶ ሄደ፡፡ ነህምያ የቆየው ለጥቂት ወራት ቢሆንም ኤልያሴብ የተባለው ታላቁ ካህን በእግዚአብሔር ቤት ለዕጣን፣ ለመባእ፣ የተለያዩ ስጦታዎችም ማስቀመጫ አድርገው የሚጠቀሙበትን ዕቃ ቤት ለማይገባው ሰው ለጦብያ የራሱ መጋዘን እንዲሆነው አድርጎ ሰጠው፡፡
- አሞናዊው አለቃ ጦብያ ከሦስቱ ክፉ ሰዎች አንዱ ነበር፡፡ ሦስቱም ሰዎች ሖሮናዊው ሰንባላጥ፣ አሞናዊው ጦብያና ዓረባዊው ጌሳም ነበሩ፡፡
- ኤልያሴብ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ሲል ሃይማኖታዊውን ሥፍራ ሸጧል፤ የተቀደሰውም ቦታ ክብር በሰው ዓይን ፊት እንዲቀል አድርጓልና የሠራው ጥፋት ማንኛውም ሰው ከሚያደርገው የከፋ ነገር ነበር፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

- ነህምያም የሆነውን ባወቀ ጊዜ በመቆጣት የጦብያ የሆኑትን ቁሳቁስ ሁሉ አስወጥቶ ልክ ጌታችን እንዳደረገው በማጽዳት ‹‹ወደ መቅደስም ገብቶ በእርሱ የሚሸጡትን የሚገዙትንም ያወጣ ጀመር፤ እርሱም፦ ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል ተብሎ ተጽፎአል፤ እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት አላቸው።›› ***ሉቃ 19፡45-46፡፡*** ቤቱን መልሶ የቀድሞውን የከበረ አገልግሎት እንዲሰጥ አደረገ፡፡
- ‹‹ለሌዋውያንም እድል ፈንታቸው እንዳልተሰጠ፥ የሚያገለግሉትም ሌዋውያንና መዘምራን እያንዳንዱ ወደ እርሻው እንደ ሄዱ ተመለከትሁ።›› ***ነህ 13፡10፡፡***
- ነህምያ ለጥቂት ጊዜ ዘወር ቢል ቀድመው ይፈሩትና ያከብሩት የነበሩት እውነትን መደራደሪያ አደረጓት፡፡ ለሌዋውያኑ ሊሰጥ የሚገባውን አስቀርተው ነበርና ሌዋውያኑ የመቅደሱን አገልግሎት ትተው የቀድሞ ሥራቸውን ለመሥራት ወደ እርሻቸው ተመለሱ፡፡ ነህምያ ሁለት ዓመት የደከመበትን ባለመኖሩ የተነሣ ሊያጠፉ ተነሣሱ፡፡ ይህም ለመልካም ሥራ ቀጣይነት የጠንካራ መሪን አስፈላጊነት የሚያስገነዝብ ነው፡፡
- ‹‹እኔም። የእግዚአብሔር ቤት ስለ ምን ተተወ? ብዬ ከአለቆቹ ጋር ተከራከርሁ። ሰበሰብኋቸውም፥ በየስፍራቸውም አቆምኋቸው። ይሁዳም ሁሉ የእህሉንና የወይኑን የዘይቱንም አሥራት ወደ ዕቃ ቤቶች አመጡ። በዕቃ ቤቶችም ላይ ካህኑን ሰሌምያን፥ ጸሐፊውንም ሳዶቅን፥ ከሌዋውያኑም ፈዳያን ሾምሁ ከእነርሱም ጋር የመታንያ ልጅ የዘኩር ልጅ ሐናን ነበረ እነርሱም የታመኑ ሆነው ተገኙ፥ ሥራቸውም ለወንድሞቻቸው ማከፋፈል ነበረ።›› ***ነህ 13፡11-13፡፡***
- ነህምያ ሁሉን አስተካክሎ ካስረከባቸው በኋላ የእግዚአብሔርን ቤት ነገር ቸል ብለው እንዲሰረቅ ያበቁ አለቆችን ወቀሳቸው፡፡
- ማንም ሰው ከአንዱ ነገድ ይልቅ ለሌላው የተለየ ጥበቃ ያደርጋል ብለው እንዳይወቅሱት በይሁዳ (በራሱ) ነገድም ሁሉን ነገር እንደገና ማስተካከል ጀመረ፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

- የይሁዳ ነገድም ካላቸው ካሥር አንዱን እጅ ለሌዋውያን ሰጡ፤ ይህንም ለሌዋውያኑ የሚገባውን በአግባብ እኩል የሚያከፋፍሉ ‹‹እምነት የሚጣልባቸው›› ናቸው የሚባሉ ሰዎችን በመምረጥ አከፋፈለ፡፡
- ‹‹አምላኬ ሆይ፥ ስለዚህ አስበኝ ለአምላኬም ቤት ያደረግሁትን ወረታዬን አታጥፋ።›› ***ነህ 13፡14፡፡*** ይህም ***በነህ 5፡19*** የተባለ ነበር፡፡ ይህ ጸሎት እግዚአብሔር ወረታውን እንዳያጠፋበት ከሚመኝ በልቡ ትሑት ከሆነ አገልጋይ የቀረበ ጸሎት (ልመና) ነው፡፡
- በእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው (እንደኔ አገልግሎቱ ታናሽም) ቢሆን ሥራው አይረሳበትም እግዚብሔር ዋጋውን ይከፍለዋልና፡፡ የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ብዙ አገልጋዮች ያስፈልጉታል እንጂ ጌታችን ‹‹መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፡፡›› ***ማቴ 9፡37፡፡*** እንዳለን ብዙ አገልጋዮች አሉ የሚባልበትም አይደለም፡፡
- ‹‹በዚያም ወራት በይሁዳ በሰንበት ቀን የወይን መጥመቂያን የሚረግጡትን፥ ነዶም የሚከምሩትን፥ የወይኑን ጠጅና የወይኑን ዘለላ በለሱንም ልዩ ልዩም ዓይነት ሸክም በአህዮች ላይ የሚጭኑትን፥ በሰንበትም ቀን ወደ ኢየሩሳሌም የሚያስገቡትን አየሁ ገበያ ባደረጉበትም ቀን አስመሰከርሁባቸው። ደግሞም በእርስዋ የተቀመጡ የጢሮስ ሰዎች ነበሩ እነርሱም ዓሣዎችን ልዩ ልዩም ዓይነት ሸቀጥ አምጥተው በሰንበት ቀን በኢየሩሳሌም ለይሁዳ ልጆች ይሸጡ ነበር። ከይሁዳም ታላላቆች ጋር ተከራከርሁና። ይህ የምታደርጉት ክፉ ነገር ምንድር ነው? የሰንበትንስ ቀን ታረክሳላችሁን? አባቶቻችሁ እንደዚህ አድርገው አልነበረምን? አምላካችንስ ይህን ክፉ ነገር ሁሉ በእኛና በዚህ ከተማ ላይ አምጥቶ አልነበረምን? እናንተም ሰንበትን በማርከሳችሁ በእስራኤል ላይ መዓትን ትጨምራላችሁ አልኋቸው።›› ***ነህ 13፡15-18፡፡***

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

- ነህምያ መልሶ ከሠራቸው ሥራዎች አንዱ ሰንበትን እንደሚገባ እንዲያከብሩ ማድረጉ ነው፡፡
- አይሁድ በሰንበት ቀን የወይን መጥመቂያን ሲያስረግጡ፥ ነዶም ሲያስከምሩ፣ የወይኑን ጠጅና የወይኑን ዘለላ በለሱንም ልዩ ልዩም ዓይነት ሸክም በአህዮች ላይ ሲያስጭኑ ወደ ኢየሩሳሌም ሲያስገቡ ከአይሁድ ወገን ያልሆኑ የጢሮስ ሰዎች በሰንበት ከሚገኝ ከዚህ ትርፍ ሲካፈሉ ጥቅማቸውንም ሲያሳድዱ አገኛቸው፡፡
- በዚህ ሥራ የተገኙትን ሁሉ አባቶቻቸው ሰንበትን በመሻር የእግዚአብሔር ቁጣ እንዴት እንደመጣባቸው እነርሱም ይህንኑ እየደገሙ መሆኑንና ይህም የሚያስከትልባቸውን ለመቀበል የተዘጋጁ መሆኑን በመግለጽ ወቀሳቸው፡፡
- ሰንበት የእግዚአብሔር ቀን ናትና ሰንበትን ማክበር ልንጠብቀው የሚገባ ትእዛዝ ነው፡፡ ሰንበት የእግዚአብሔር ቀን፣ ቅዳሴ የምናስቀድስባት፣ ቅዱስ ቁርባን የምንቀበልባል፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው መጻሐፍት የሚነበቡባት፣ እግዚአብሔርም የሚገለገልባት ቀን ሆና ትቀጥላለች፡፡
- ‹‹ከዚህ በኋላ ከሰንበት በፊት በኢየሩሳሌም በሮች ድንግዝግዝታ በሆነ ጊዜ በሮችዋ እንዲዘጉ፥ ሰንበትም እስኪያልፍ ድረስ እንዳይከፈቱ አዘዝሁ። በሰንበትም ቀን ሸክም እንዳይገባ ከብላቴኖቼ በአያሌዎቹ በሮችዋን አስጠበቅሁ። ሁሉም አንድ ወይም ሁለት ጊዜ በኢየሩሳሌም ውጭ አድረው ገበያ አድርገው ነበር። እኔም አስመሰከርሁባቸውና። በቅጥሩ ውጭ ለምን ታድራላችሁ? እንደ ገና ብታደርጉት እጆቼን እነሣባችኋለሁ አልኋቸው። ከዚያም ወዲያ በሰንበት ቀን እንደ ገና አልመጡም። ሌዋውያኑንም ራሳቸውን እንዲያነጹ፥ መጥተውም በሮቹን እንዲጠብቁ፥ የሰንበትንም ቀን እንዲቀድሱ ነገርኋቸው። አምላኬ ሆይ፥ ስለዚህ ደግሞ አስበኝ፥ እንደ ምሕረትህም ብዛት ራራልኝ።›› ***ነሀ 13፡19-22፡፡***

# <u>መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲</u>

- ነህምያ ብርቱና ደፋር ነበርና ጠባቂዎችና መልእክተኞች ዓርብ ቀን ከሥርክ አንስቶ ሁሉንም በሮች ለሃያ አራት ሰዓታት እንዲዘጉ አዘዘ። በቀዳሚት ሰንበት ማንም ማን እንዳይገባና እንዳይወጣ ተደረገ።
- በሰንበትም ቀን ሲሸጡና ሲለውጡ ሰንበትንም ሲሽሩ የነበሩ ለሃያ አራት ሰዓታት እንዳይገቡ ተከለከሉ። ይህም ለጥቂት ሳምንታት ቀጠለ፤ በደጅ ሆነው የሚጠብቁ ካሉም እንደሚያስራቸው ስላስጠነቀቃቸው ትእዛዙን አክብረው ተቀበሉ።
- ሌዋውያንም በሮቹን እንዲጠብቁና ሰንበትንም ሳይገዙና ሳይሸጡ የተቀደሰች ዕለት አድርገው እንዲያከብሩ አዘዛቸው።
- ‹‹አምላኬ ሆይ፥ ስለዚህ ደግሞ አስበኝ፥ እንደ ምሕረትህም ብዛት ራራልኝ።›› በማለትም ልቡናውን ወደ እግዚአብሔር በማንሳት ሰንበትን ለማክበር የእግዚአብሔርን እርዳታ ጠየቀ። በዚህም ሳይኮራና ሳይመካ የታመነውን ልብ ይዞ ለንስሐ ራሱን አዘጋጅቶ አቀረበ።
- ‹‹ደግሞም በዚያ ወራት የአዛጦንና የአሞንን የሞዓብንም ሴቶች ያገቡትን አይሁድ አየሁ። ከልጆቻቸውም እኩሌቶቹ በአዛጦን ቋንቋ ይናገሩ ነበር፥ በአይሁድም ቋንቋ መናገር አያውቁም ነበር።›› ***<u>ነህ 13፡23-24።</u>***
- አዛጦን ከፍልስጥኤም ከተሞች አንድዋ ስትሆን ነህምያ አንዳንድ ከአይሁድ ወገን የሆኑ ከአሕዛብ (ካላመኑት) ከአዛጦን፣ ከሞዓብና ከአሞን ሴቶች ወስደው እንዳገቡና አብረውም እንደሚኖሩ፣ ከሁሉም በላይ የጥንት የአይሁድን ቋንቋ መጠቀምን ረስተው በአህዛብ ቋንቋ እየተጠቀሙ የገዛ ራሳቸውን ቋንቋ ረስተዋልና በዚህም በኩል የነበረባቸውን ችግር አስተካከለ።
- በርግጥ ዛሬም ብዙዎች ለራሳችን ቋንቋ (ግዕዝ) አላዋቂ ስለሆን የዓለምን ቋንቋና ስታይል (ይትበሃል/ዘይቤ) ስንጠቀም እንገኛለን።

# <u>መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲</u>

- ‹‹ከእነርሱም ጋር ተከራከርሁ፥ ረገምኋቸውም ከእነርሱም አያሌዎቹን መታሁ፥ ጠጉራቸውንም ነጬሁ፥ እንዲህም ብዬ በእግዚአብሔር አማልኋቸው። ሴቶች ልጆቻችሁን ለወንዶች ልጆቻቸው አትስጡ፥ ሴቶች ልጆቻቸውንም ለእናንተና ለልጆቻችሁ አትውሰዱ። የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞን በዚህ ነገር ኃጢአት አድርጎ የለምን? በብዙ አሕዛብም መካከል እንደ እርሱ ያለ ንጉሥ አልነበረም፥ በአምላኩም ዘንድ የተወደደ ነበረ፥ እግዚአብሔርም በእስራኤል ሁሉ ላይ አንግሦት ነበር እርሱንም እንኳ እንግዶች ሴቶች አሳቱት። በውኑ ይህን ሁሉ ታላቅ ክፉት እንሠራ፥ እንግዶችንም ሴቶች በማግባት አምላካችን እንበድል ዘንድ እናንተን እንስማ?›› ***<u>ነህ 13፡25-27፡፡</u>***
- **አይሁድ ከዚህ ዓለም ሰዎች ጋር እየኖሩ፣ ቋንቋቸውን እየተናገሩ፣ በጎ ምግባራቸውን አጥፍተው የአሕዛብን ምግባር እየወረሱ፣ ሃይማኖታቸውንና ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ቃል ኪዳን (መሐላ) አጥፍተው ቢያገኛቸው ስለ እስራኤል ንጉሥ ስለ ሰሎሞን አስታወሳቸው፡፡ ንጉሥ ሰሎሞን እንደርሱ ያለ በእግዚአብሔር የተወደደ ያለ ባልነበረበት የነበረ፣ እጅግ መንፈሳዊ፣ ጥበበኛና የጥበብ መጻሕፍትንም የጻፈ ቢሆንም ወደ ዘመኑ ፍጻሜ ተመሳሳይ ኃጢአት ሠራ፤ ከአህዛብ ሴቶች ወስዶ ለራሱ አደረጋቸው፣ እነዚያም ሴቶች ልቡናውን እግዚአብሔርን ከማምለክ እንዲሸፍት አደረጉት - ጣዖት አስመልከው በኃጢአቱ ለጥፋት ቢያደርሱትም እግዚአብሔር ግን በቅዱስ ዳዊት አማላጅነት!!! ንስሐ ለመግባት አበቃው፡፡ አማላጅነት!!!**
- ‹‹ከዋነኛውም ካህን ከኤልያሴብ ልጅ ከዮአዳ ልጆች አንዱ ለሖሮናዊው ለሰንባላጥ አማች ነበረ ከእኔም ዘንድ አባረርሁት። አምላኬ ሆይ፥ ክህነትን የክህነትንና የሌዋውያንንም ቃል ኪዳን ስላፈረሱ አስባቸው።›› ***<u>ነህ 13፡28-29፡፡</u>***
- **በቅስና (በክህነት) አገልግሎትም ቢሆን ሙልጭልጭ መሆን አይፈቀድም፡፡ በዚህም የተነሳ ነህምያ ከታላቁ ካህን ከኤልያሴብ ልጆች ወይም ከልጅ ልጆቹ አንዱ ለሖሮናዊው ሰንባላጥ አማች እንደሆነ ሲያውቅ አባረረው  ታላቁ ካህን ኤልያሴብ ራሱ የተበላሸና ብልሹ አሠራር የነበረው ነውና፡፡**

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

- ‹‹ከእንግዳ ነገርም ሁሉ አነጻኋቸው ለካህናቱና ለሌዋውያኑም እያንዳንዳቸው በየሰሞናቸው፥ በየጊዜያቸውም ለእንጨት ቍርባን ለበኵራቱም ሥርዓት አደረግሁ። አምላኬ ሆይ፥ በመልካም አስበኝ።›› ***ነህ 13:30-31:***
- **ነህምያ ተራ አገልጋይ ነበር እንጂ ካህን ወይም ሊቀ ካህን ባይሆንም እግዚአብሔርንና ቤተ (መቅደሱን) ክርስቲያንን እጅግ በጥልቀት ስለ ወደደ በርሱ የትውልድ ዘመን ማንም ሊቀዳጀው የማይችለውን ውጤት ተቀዳጅቷል፡፡**
- **እየንዳንዳችን የነህምያ ልብ ካለን ብዙ ነገሮችን ማስተካከል እንችላለን፤ ይልቁንም ምንም ይሁን ምን በመጽሐፍ ቅዱስ የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ቃል አክብረን ከያዝን ቤተ ክርስቲያን ዳግመኛ ትጠነክራለች ቅጥሮችም ይኖሩአታል፡፡**
- **በብርቱ ጸሎት የሚተጋው፣ አማኙ፣ ጠንካራ ሠራተኛ የሆነው ነህምያ ለወገኖቹና ለአገሩ እንጂ ለራሱ ብቻ የሚበጀውን ከቶ አላሰበም፡፡**
- **እኛም እንዲህ ያለ መንፈስ ከያዝን ቤተ ክርስቲያን ወደ ጥንካሬዋና ውበትዋ ተመልሳ ስህተት የሌለበት አገልግሎትዋን ትቀጥላለች፡፡**
- ‹‹እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ።›› ***ኤፌ 5:27::*** **እንዳለው ለክርስቶስ የምታስፈልገው እርስዋ ናትና፡፡**
- **በቃል የሚጠኑ ጥቅሶች፡-**
- ‹‹አምላኬ ሆይ፥ ስለዚህ አስበኝ ለአምላኬም ቤት ያደረግሁትን ወረታዬን አታጥፋ። ›› ***ነህ 13:14::***
- ‹‹አምላኬ ሆይ፥ ስለዚህ ደግሞ አስበኝ፥ እንደ ምሕረትህም ብዛት ራራልኝ።›› ***ነህ 13:22::***
- ‹‹አምላኬ ሆይ፥ ስለዚህ ደግሞ አስበኝ፥ እንደ ምሕረትህም ብዛት ራራልኝ።›› ***ነህ 13:31::***

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

## ማጠቃለያ 1

- መጽሐፈ ነህምያ የተጻፈው 420 ከክ.ል.በፊት ነው። ነህምያ የነበረውም በኢራን - ፋርስ (ሱሳ) ነበር። ወደ ኢየሩሳሌም የመጣውም በባቢሎን (ኢራቅ)ና በሶርያ አቋርጦ ነበር። ነህምያ ማለት እግዚአብሔር መጽናኛ ነው ወይም መጽናኛ አለው ማለት ነው።
- ወደ ኢየሩሳሌም የተመለሱትን እስራኤላውያን መርቶ ወደ ከተማይቱ የተመለሰ በፋርስ ንጉሥ ዘንድ የጠጅ አሳላፊ የነበረ ለወገኖቹ፣ ለአገሩና ለሃይማኖቱ የሚቆረቆር ነበር።
- በመጽሐፈ ነህምያ ቅጥሩ፣ ቤተ መቅደሱ፣ ቃል ኪዳኑ (ውሉ)፣ ሕዝቡ ተመልሰው እንደታነጹ እንማራለን።
- ነህምያ ከእግዚአብሔር የሆነ መሪ ስለሆነ፦
    - ለእያንዳንዱ ነገር ጥልቅ ትኩረት ያደርግ ነበር፣
    - ለወገኖቹ ይቆረቆር ነበር፣
    - ለአምላኩና፣ ለሃይማኖቱና ለአምልኮቱ ይቆረቆር ነበር፣
    - በጸሎት የተጋ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግኑኝነት የነበረው ነበር፣
    - ለእግዚአብሔር ታላቅ ክብር የሚሰጥ የአገልጋይ ልቦና ያለው ነበር፣
    - በግሉ ኃላፊነትን መውሰድ የሚችል ለንስሐ የተዘጋጀ ልቦና የነበረው ነው፣
    - የእግዚአብሔርን ቃል የሚያውቅ ትእዛዙንም የሚጠብቅና በተግባር የሚኖርበትም ነበር፣
    - ሲቸግረው ወዴት እንዳለበት የሚያውቅ፣ የምቾት ኑሮውን ለአገልግሎት ሲል የተወ፣
    - ሥራውን በፍጹም ውጤታማነት የሚያከናውን፣ የሌላውን መብትና ሥልጣን ብሎም ሕግን የሚያከብር፣
    - እንቅፋቶቹንና ጠላቶቹን የሚያውቅ፣ ማንኛውንም ነገር በትክክለኛው መንገድ ብቻ እየሠራ አስተያየቶችንም በአግባብ የሚገመግማቸው፣ በውስጥም ሆነ በውጭ የሚገጥሙትን ተቃውሞች ተቋቁሞ ዓላማውን የሚያሳካና ግቡን የሚመታ፣

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

## ማጠቃለያ 1

- ነገሮችን ሁሉ በጥልቀት የሚመረምራቸው፣ ላገኘው ሁሉን የማያወራ - ልከኛ፣ ችግሮችን በአግባቡ መመልከት የሚችል፣ ዕድል እንዳታመልጠው የሚጠነቀቅ፣ በችግሮችና ፈተናዎች ተስፋ የማይቆርጥ፣ አብሮ ለመሥራት ማስተባበር የሚችል ሕዝቡንም የሚያበረታታ፣ በእግዚአብሔር ያለውን እምነት ያጸና ክብርንም ለእግዚአብሔር የሚሰጥ፣
- የአገልጋዮችን ልቦና የሚጠብቅ፣ ጠላቶቹ ምንም ቢበዙ ከግቡ ዝንፍ የማይል፣
- ለሕዝቡ የተሰጠውን ስጦታ ለይቶ አውቆ እንደተሰጥዖአቸው ማሰለፍ የሚችል፣
- ሥራን ከግልጽ ዓላማው ጋር ማስረከብን፣ መከታተልንና ውጤት መቀበልን የሚያውቅ፣
- ማን ምን እንደሠራ የሚከታተል፣ ያልሠራውም ማን እንደሆነ የሚለይ የሚያበረታታም፣
- የሰው ኃይል አቅሙን በአግባቡ የሚጠቀም፣ ሕዝቡንም የሚንከባከብና የሚጠብቅ፣
- ለአደጋ ጊዜ በቂ ዝግጅት ያደረገ፣ በሥራና በሥልጣን ክፍፍል የሚያምን፣ ትክክለኛ የእዝ መሥመር ያለው፣
- ችግሮቹን ለይቶ በማውጣት የሚጋፈጣቸው፣ ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲፈሩ የሚያስታውሳቸው፣
- በሕዝቡ ላይ ጥቃት እንዲፈጸም የማይፈቅድ፣ በአጋጣሚዎች ሕዝቡን ጎድቶ ራሱን የማይጠቅም፣
- ሥራውን ጠንቅቆ የሚወጣ፣ ስም አጥፊዎችንና ሥራ ፈቶችን የማይፈራ፣ በወጥመድ የማይጠለፍ፣
- ለእግዚአብሔር ክብርን በመስጠት ተልእኮውን በብቃት የፈጸመ፣ በመንፈሱ ትሑት የሆነ፣
- ከባድ ፈተናዎችን በትዕግሥትና በጸሎት መጋፈጥን፣ ሥራን በዕቅድ መምራትን፣ የጀመርነውን ሥራ ሳናቋርጥ መቀጠልን፣ በበጎ ነገሮች ሁሉ ተሳታፊ መሆንን፣ በጎ ነገሮች እንዳይጠፉ መንከባከብን፣ መልካም መሠረት መጣልን፣ በቅን የሚሠሩ ሥራዎችን በአእምሮ ተልሞ ማዘጋጀትን፣ ለሥራ የሚያስፈልጉንን ሁሉ ለይቶ ማወቅን የምንማርበት መልካም መሪ ነበር።

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

## ማጠቃለያ 2

- መጽሐፈ ነህምያ ከምዕራፍ አንድ እስከ አሥራ ሦስት ድረስ አሥራ ሁለት የአመራርን መርሆዎችን ተምረናል፡፡ እነርሱም፡-
    1. እንድንሠራለት የወደደውንና የገለጠልንን የእግዚአብሔን ሥራ ትኩረት ሰጥተን መሥራት፡፡ ነህ 2፡12
    2. ሥራችንን በጸሎት መሥራት፡፡ ነህ 1፡4-11፡፡
    3. ለሥራው የሚመጥን ሥነ ምግባር ይዞ መገኘት፡፡ ነህ 2፡1-8፡፡
    4. በዘረጋነው ሥርዓት ሥር ሆነን መሥራት፡፡ ነህ 2፡1-8፡፡
    5. ተቃውሞ እንደሚገጥመን እንጠብቅ እንጂ አንደንግጥ፡፡ ነህ 2፡9-11፡፡
    6. ሥራውን በጥንቃቄ አስበን፣ አቅደንና ተዘጋጅተን እንሥራ፡፡
    7. በሚፈለገው ነገርና በአዘጀነው እቅድ ላይ ምክክር እናድርግ፡፡ ነህ 2፡17-18፡፡
    8. ሥራውንና በሥራው የሚገኘውን አክብሮት ሥራውን ከሠሩት ሁሉ ጋር መጋራት፡፡ ነህ 3፡፡
    9. የእግዚአብሔር ኃይል እንቅፋቶቹንና ችግሮቹን ሁሉ እንደሚያስወግድና እንደሚፈታ እንመን፡፡ ነህ 4፡፡
    10. እግዚአብሔር እንዲከራከርላችሁ ሁኑ፡፡ ነህ 6፡፡
    11. ፍትሕን ማስከበር፡፡ ነህ 5፡፡
    12. የጀመርነውን ሥራ ማጠናቀቅ ወይም መፈጸምን ተምረናል፡፡

- ***አስጀምሮ ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይሁን፡፡ አሜን፡፡***

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org